# SY25-26 እና SY26-27 Phelps የአርክቴክቸር፣ ኮንስትራክሽን እና ምህንድስና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የቅበላ ሂደት ስሌት

ለክፍል፡ 9-11

**ማስታወሻ፥** ይህ መመርያ ለSY25-26 እና SY26-27 የተማሪ ቅበላ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**ስለ Phelps ACE ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የቅበላ መስፈርት**: በPhelps ACE ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ችግር ፈቺ የሆኑ፣ በኛ የCareer Technical Education ፕሮግራም ላይ ፍላጎት ያላቸው እና መፍትሄዎችን ለማግኘት በፈታኝ ተግዳራቶች ውስጥ የመስራት ፍላጎት ያላቸውን ምሁራን ማግኘት እንፈልጋለን። በጣም ስኬታማ የሆኑት አመልካቾች ውጤታቸው ጥሩ ባይሆንም በትምህርታቸው ላይ ተገቢውን ጥረት የሚያደርጉት ሆነው አግኝተናቸዋል።

**ስለ Phelps ACE ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የቅበላ ሂደት**: በPhelps ACE High School የቅበላ ሂደታችን ጽሁፍን፣ አንድ ቃለ መጠይቅን እና በMy School DC መተግበርያ የቀረቡ ሁለት የድጋፍ ደብዳቤዎችን ያካትታል። ለማንኛውም አመልካች እያንዳንዱን የቅበላ ክፍል ታሳቢ የምናደርግ ሲሆን ሁሉም አመልካቾች በተቀመጠ መስፈርት መሰረት ውጤት ተሰጥቷቸዋል። የትኛውም አንድ የቅበላ መስፈርት ወይም ክፍል ብቃትን ለመወሰን ብቸኛ መለኪያ አይሆንም። ለቅበላ ከግምት ውስጥ ለመግባት ሁሉም አመልካቾች ቃለ መጠይቅ ማድረግ አለባቸው።

እያንዳንዱ ክፍል ከታች ባለው ሰንጠረዥ መሰረት ውጤት ተሰጥቶት ይመዘናል። ለቅበላ ከግምት ውስጥ ለመግባት አመልካቾች በድምሩ ቢያንስ 15 ነጥብ ማግኘት አለባቸው። ከዚህ በታች ያመጡ አመልካቾችም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ብቁ የሆኑ አመልካቾች በሙሉ ባገኙት ጠቅላላ ነጥብ መሰረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።

| የቅበላ ክፍል | ክብደት | ማሳሰቢያዎች |
|---|---|---|
| የትምህርት መስፈርት ግምገማ (GPA እና ተሳትፎን ይጨምራል) | 12/30 ነጥብ | Phelps ACE ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደ የሪፖርት ካርድ ግምገማ አንድ አካል ሆኖ የትምህርት ውጤቶችን (GPA) እና ተሳትፎ ይገመግማል። የ SY23-24 የመጨረሻ እና የ SY24-25 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርት ካርዶች መቅረባ አለባቸው። የሚፈለግ ዝቅተኛ GPA ወይም የተሳትፎ ቀን የለም፣ ነገር ግን ሁለቱም የሪፖርት ካርዶች መቅረብ አለባቸው። የሚመከረው ዝቅተኛው GPA 2.5 ነው<br><br>ምንም እንኳን በተገቢው ድጋፍ እና ስልት ስኬታማ መሆን የቻሉ በዝቅተኛ GPAs የገቡ በርካታ አመልካቾች ያሉን ቢሆንም፣ በዋናነት በኛ ፕሮግራም ውስጥ ስኬታማ የሆኑ አመልካቾች በሰዓት መቆጣጠርያ ወይም በትምህርት ክትትል 90% ወይም ከዚያ በላይ አላቸው። |

| | | |
|---|---|---|
| ቃለ መጠይቅ | 12/30 ነጥብ | Phelps ACE ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በኛ CTE ፕሮግራሞች ላይ እውነተኛ ፍላጎት ያላቸውን እና ችግሮችን የመፍታት ከፍተኛ ፈቃደኝነት ያላቸውን አመልካቾች ላይቶ በማወቅ በጥብቅ ያምናል። ከወደፊት ተማሪዎቻችን ጋር የምንገናኝበትን ይህን እድል የምናከብረው ሲሆን የቃለ መጠይቁ ሂደት ይህን ለማሳካት ውጤታማ መንገድ ሆኖ ያገለግላል። የወደፊት አመልካቾችን ማወቅ የምንፈልግ ሲሆን ይህን ለማድረግ ቃለ መጠይቁ ጥሩ መንገድ ነው።<br><br>አመልካቾች ቃለ መጠይቁ ላይ ከቤተሰብ አባል (ወላጅ፣ ህጋዊ አሳዳጊ ወይም ሌላ ቅርብ የቤተሰብ አባል ጋር) ወይም ተማሪውን በመደበኛነት ከሚያግዝ ሌላ አስፈላጊ ሰው (አሰልጣኝ፣ አማካሪ ወይም አስጠኚ) ጋር እንዲቀርቡ እንጠይቃለን።<br><br>በአመልካች ቃለ መጠይቅ ወቅት፣ አብሮት የሚገኘው አዋቂ ሰው ትምህርት ቤቱን መጎብኘት ወይም ከአመልካች አምባሳደሮች እና/ወይም የPTO አባላት ጋር በሚደረግ ጥያቄና መልስ ላይ መሳተፍ ይችላል። አመልካቹን አጅቦ የሚገኘው አዋቂ ተሳትፎ ውጤት ለመስጠት በማናቸውም ሁኔታ ታሳቢ አይደረግም።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ምክንያቶች፣ ለ SY25-26. ቃለመጠይቆች በኦንላይን ሊደረጉ ይችላሉ። |
| በቦታው በመገኘት የሚቀርብ የጽሁፍ ናሙና (በቃለ መጠይቁ ወቀት የሚሞላ) | 3/30 ነጥብ | ልክ እንደ ቃለ መጠይቁ ሁሉ፣ የሮፍ ድጋፉም አመልካች በኛ ፕሮግራሞች ላይ ያለውን ፍላጎት እና የጽሁፍ ተግባቦት ክህሎቱን ለመመዘን ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ ድጋፍ የቃለ መጠይቁ አካል ተደርጎ በቦታው ይሞላል።<br><br>ምንም እንኳን አመልካቾች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቆይታቸው ሁሉ ውስጥ በመደበኝነት እንደሚጽፉ የሚጠበቅ ቢሆንም፣ የዚህ ድጋፍ መስፈርት እንደ ሰዋወሰው እና ቃላት ባሉት ቴክኒካዊ የጽሁፍ ክህሎቶች ላይ አያተኩርም። የጽሁፍ ናሙናው የሚያተኩረው የCTE አላማዎችን በግልጽ በመረዳት እና ለስራ ተኮር ትምህርት እውነተኛ ፍላጎት ማሳየት ላይ ነው። በተጨማሪም ናሙናው ትምህርታዊ ተግዳሮቶችን ለመፍታት እና በፈጠራ የተሞሉ መፍትሄዎችን ለማምጣት ያሉ ተንታኝ ክህሎቶችን አጉልቶ በማሳየት አመልካቹ ያለውን በጥልቀት የማሰብ እና ችግሮችን የመፍታት ችሎታዎች ያሳያል።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ምክንያቶች፣ ቃለመጠይቆች (በምዘና ቦታው ላይ የጽሑፍ ናሙና ማጠናቀቅን ይጨምራል) ለ SY25-26 በኦንላይን ሊደረጉ ይችላሉ። |
| የድጋፍ ደብዳቤዎች | 3/30 ነጥብ | Phelps ACE ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አመልካቹ በትምህርት ቤት ስላለው ልምድ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት እና ለውጤት መግለጫ ካርዳቸው አውድ ለመስጠት የድጋፍ ደብዳቤዎችን ይጠቀማል።<br><br>ሁለት (2) የድጋፍ ደብዳቤ/ሪኮመንዴሽን ያስፈልጋል። በተጠየቀው መምህር የተሞላው አንድ ብቻ ከሆነ፣ አመልካቹ በቀረበው አንድ የድጋፍ ደብዳቤ ብቻ እንመዝነዋለን። በዚህ ክፍል ሙሉ ነጥብ ለማግኘት አንድ የድጋፍ ደብዳቤ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ማቅረብ በቂ ነው። ይሁን እንጂ የድጋፍ ደብዳቤዎች ካልቀረቡ፣ ለቃለ መጠይቅ በተመደበው ክብደት ላይ 1 ነጥብ ይደመራል። |
| **ለቅበላ ከግምት ውስጥ ለመግባት አመልካቾች በድምሩ ቢያንስ 15 ነጥብ ማግኘት አለባቸው። ብቁ የሆኑ አመልካቾች በሙሉ ባገኙት ጠቅላላ ነጥብ መሰረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።** | | |